# አድርገህልኛልና

አድርገህልኛልና በቸርነትህ አመሰግንሃለሁ እልል እልል (2)
ለዓለመ ዓለም አማኑኤል እገዛልሃለሁ መድኃኔዓለም (2)

ቀኑ ጨልሞብኝ ዙሪያው ገደል ሆኖ
የችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ
ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ
ፈጽሞ አራቅህልኝ የልቤን ትካዜ
አዝ...

አምላኬ ጉልበቴ ኃይሌ መመኪያዬ
ጠላት ማሳፈሪያ የእምነት ጋሻዬ
እንደማትተወኝ አሁን አውቄአለሁ
ካለኝ ነገር ይልቅ ባንተ ታምኛለሁ
አዝ...

ጥቂቷን አብዝተህ ለምትመግብ ጌታ
የምመልስልህ ባላገኝ ሥጦታ
በቀንም በሌሊትም ሁሌ ለሚያበራ
መንክር ለባሕርይህ ዕጹብ ለአንተ ሥራ
አዝ...

አምላክ ሆይ ምስጋና ለአንተ ይገባሃል
ለምስኪኗ ጎጆ በረከት ሰጥተሃል
ድሃ ነኝ አልልም ሀብቴ አንተ ነህና
ማሰሮዬ ሞልቷል ላይጎድል እንደገና
አዝ...